**የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ፍትህ ቢሮ**
Central Ethiopia Region State Justice Bureau

ቁጥር 0024/24/5269
ቀን 05/05/2017

**ለማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሳይንስ እና ኢንፎርሜሽን ቢሮ**

**ወራቤ**

**ጉዳዩ፡- <u>የተመዘገበ መመሪያ መላክን ይመለከታል</u>**

ከመግቢያው ለመግለጽ እንደተሞከረው ቢሯችሁ በቁጥር ማ/ኢ/ሳ/ኢ/ቴ/ቢ0078/01/11-115 በቀን 21/04/2017 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ ከዚህ ቀደም ሲጠቀምበት የነበረውን የሳይንስ ካፌዎች አደረጃጀት እና አስተዳደር የአሰራር መመሪያን እንዲመዘገብልን በማለት መጠየቃችሁ ይታወቃል፡፡

በዚህ መሰረት ከተቋማችሁ የመጣውን መመሪያ በጥልቀት ፈትሸን በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት የአስተዳደር ሥነ ስርአት አዋጅ ቁጥር 23/2016 አንቀጽ 16/2/ መሰረት በዛሬው ቀን ማለትም ጥር 5/2017 ዓ/ም " **የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ሳይንስ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ ያወጣውን የሳይንስ ካፌዎች አደረጃጀት እና አስተዳደር የአሰራር መመሪያ ቁጥር 08/2017 ዓ.ም** "ሆኖ የተመዘገበ መሆኑን እየገለጽን በክልሉ የአስተዳደር ሥነስርአት አዋጅ ቁጥር 23/2016 አንቀጽ 17/4/ መሰረት ተቋማችሁ መመሪያውን ተደራሽ ለማድረግ እንዲቻል ለተጠቃሚዎች በመመሪያው ይዘት ላይ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ እንዲሰራ 1መሪያው ስካን ተደርጎ በፒዲኤፍ ፎርማት በቢሯችሁ ድረ ገጽ ላይ እንዲጫን እንዲሁም መመሪያውን በማሳተም ለሚመለከታቸው መንግስታዊ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት እንዲሰራጭ ወይም ማንኛውም የመመሪያ ቅጅ ማግኘት ለሚፈልግ ሰው መመሪያውን ባለበት ሁኔታ የመመልከት ወይም ወጪውንሸፍኖ ከቢሯችሁ እንዲያገኝ እንዲደረግ እያሳሰብን <u>19</u> ገጽ የያዘውን መመሪያ በዚህ ደብዳቤ ሸኝነት የላክን መሆናችንን እንገልፃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

አክመል አህመዲን ሶማ
Akmel Ahmedin Soma
የፍትህ ቢሮ ኃላፊ
Head of Justice Bureau

**<u>ግልባጭ</u>**

- ለቢሮ ኃላፊ ጽ/ቤት
- ለህግ ጉዳዮች ዘርፍ
- ለህግ ጥ/ማ/ማ/ ዳይሬክቶሬት

ፖ/ሳ የመ.ሣ.ቁ 291
P.O. Box

ስ.ቁ 046 220 58 00
Tel

ፋክስ- 046 221 24 37
Fax

email:- justicebureauplan@gmail.com

ፍትህ ለሁሉም!!!/Justice for All!!!

# የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት

## ማዕከላዊ ነጋሪት ጋዜጣ

## MAEKELAWI NEGARIT GAZETA

## OF THE CENTRAL ETHIOPIA REGIONAL STATE


| | | |
|---|---|---|
| ወራቤ 2ኛ ዓመት ቁጥር--<br>ታህሳስ____ 2017 ዓ.ም | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት<br>ጠባቂነት የወጣ | Worabe 2nd Year No--<br>December _/2024 |


## የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የሳይንስ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ

«የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት የሳይንስ ካፌዎች አደረጃጀትና አስተዳደር የአሰራር መመሪያ ቁጥር 08 -/2017«

# መግቢያ

በክልሉ የሚካሔዱ የሳይንስ ካፌ አደረጃጀትና አስተዳደር ስራዎች ወጥና ፍትሐዊ አሰራርን የተከተሉ እንዲሆኑና አጠቃቀማቸውም የታለመላቸውን ዓላማ መሠረት ባደረገ መልኩ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፤

በክልላችን ካለው የአጠቃላይ ሕዝብ ቁጥር አብዛኛው ወጣቱ ክፍል መሆኑና ይህም ምርታማ የህብረተሰብ ክፍል ቁጥር እየጨመረ ያለ እንደመሆኑ መጠን ይህን ኃይል የሳይንስ ባህሉን፤ አስተሳሰቡን እና የስራ ፈጠራውን በማጎልበት ጥቅም ላይ ማዋል በማስፈለጉ፤

ወጣቱ ኃይል ስለ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ የሚወያይበት፤ ቴክኖሎጂዎች እንዴት እንደሚሰሩ ልምድ የሚቀስምበት፤ የስራ ፈጠራ ሃሳቦችን የሚያገኝበት እና እየተዝናና የሚማርበት የሳይንስና ቴክኖሎጂ መሰረት ልማቶች ውስን በመሆናቸው፤

የክልሉ ሕብረተሰብ ከሳይንሳዊ ማህረሰቡ ጋር የሚገናኝበት በዚህም ሳይንሳዊ አስተሳሰብና ለዘርፉ ያለውን ፍላጎት የሚያሳድግበት ስፍራ አናሳ መሆኑን በመገንዘብ፤

ከፍተኛ ባለሙያዎች  እና ተመራማሪዎች የሕብረተሰቡን ፍላጎትና ችግር የሚገነዘብበት፤ በዚህም ችግር ፈቺ የምርምር መነሻ ሃሳብ የሚያገኙበት እና የምርምር ውጤታቸውን በቀላሉ ለሕብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ የሚችሉበት ስፍራ ዝቅተኛ በመሆኑ ይህንን ችግር ደረጃ በደረጃ መቅረፍ አስፈላጊ መሆኑ በመታመኑ፤

የማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ በክልሉ የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣ አዋጅ ቁጥር 199/2015 አንቀጽ 39 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የሳይንስ ካፌዎች አደረጃጀትና አስተዳደር የአሰራር መመሪያ ቁጥር - 08 /2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### 2. ትርጓሜ

1. **"ሳይንስ "**ማለት ነባራዊውን አለም እና የተፈጥሮ ህግጋትንና ክስተቶችን ለማብራራትና ለመገንዘብ የሚያስችለንን እውቀት በምልከታና በሙከራ የምናገኝበት ዘዴ ነው::
2. **"ሳይንስ ካፌ"** ማለት ወጣቶች ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ያላቸውን ዝንባሌ በማጎልበት በንባብ፣ በኮንፈረንስና በገጽ ለገጽ ውይይቶች እንዲሁም የዕውቀትና የልምድ ልውውጥ በማድረግ ስብዕናቸውን የሚገነቡበትና ዕውቀትና ክህሎታቸውን የሚያዳብሩበት ዘመናዊ የአቅም ግንባታ ማዕከል ነው::
3. **"ክልል"** ማለት የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ማለት ነው::
4. **"መማክርት ጉባዔ"** ማለት ክልላዊ የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መማክርት ጉባዔ ነው::
5. **"ቢሮ"** ማለት በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ ነው::
6. በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተነገረው አገላለጽ ሴትንም ይጨምራል::

### 3. የሳይንስ ካፌ አስፈላጊነት፤

1. በክልላችን ካለው የአጠቃላይ ሕዝብ ቁጥር አብዛኛው ወጣቱ ክፍል መሆኑና ይህም ምርታማ የህብረተሰብ ክፍል ቁጥር እየጨመረ ያለ እንደመሆኑ መጠን ይህን ኃይል የሳይንስ ባህሉን፣ አስተሳሰቡን እና የስራ ፈጠራ ክህሎቱን ማጎልበት በማስፈለጉ፤
2. ወጣቱ ኃይል ስለ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ የሚወያይበት፣ ቴክኖሎጂዎች እንዴት እንደሚሰሩ ልምድ የሚቀስምበት፤ የስራ ፈጠራ ሃሳቦችን የሚያገኝበት እና እየተዝናና የሚማርበት የሳይንስና ቴክኖሎጂ መሰረት ልማቶች ውስን በመሆናቸው፤

3. የክልሉ ሕብረተሰብ ከሳይንሳዊ ማህረሰቡ ጋር የሚገናኝበት በዚህም ሳይንሳዊ አስተሳሰብና ለዘርፉ ያለውን ፍላጎት የሚያሳድግበት ስፍራ እናሳ መሆን፤
4. ከፍተኛ ባለሙያዎች እና ተመራማሪዎች የሕብረተሰቡን ፍላጎትና ችግር የሚገነዘቡበት፤ በዚህም ችግር ፈቺ የምርምር መነሻ ሃሳብ የሚያገኙበት እና የምርምር ውጤታቸውን በቀላሉ ለሕብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ የሚችሉበት ስፍራ ዝቅተኛ መሆን።

**4. የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች፤**

የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች የመደበኛ ትምህርት መምህራንና ተማሪዎች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የቴ/ሙ/ት/ስ ተቋማት፣ የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራዝ እንቀሳቃሾች እንዲሁም ከትምህርት ስርዓት ውጭ ያሉ ወጣቶችና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው።

**5. የሳይንስ ካፌዎች ሎጎ**

በክልሉ በየትኛውም አካባቢ የሚገነቡ የሳይንስ ካፌዎች የሚከተለውን ሎጎ የሚጠቀሙ ይሆናል።

**6. የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በክልሉ የሳይንስ ካፌ በሚገነቡባቸው አካባቢዎች፤ በግንባታ፣ አደረጃጀትና አስተዳደር ተግባራቱ ዙሪያ ተሳታፊዎችና ተዋናዮች እንዲሁም በካፌዎቹ ተገልጋይ በሚሆኑ ግለሰቦችና ተቋማት ላይ በሙሉ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

## ክፍል ሁለት

## ካፌ የሚደራጅባቸውን አካባቢዎች ስለመለየት

### 7. የፍላጎት ዳሰሳ ስለማከናወን

1. ቢሮው ካፌ ለማደራጀት የሚያስችል ሀብት ከመንግስት ወይም ከሌላ አጋር አካል ሲያገኝ ማደራጀት የሚችለውን የካፌ ቁጥር በመወሰን የሚደራጅበትን ወይም የሚደራጅባቸውን ከተሞች ከክልሉ ከተሞች መካከል መምረጥ የሚያስችል መስፈርት ያዘጋጃል፤
2. በዞኖች/ በልዩ ወረዳዎች እና ወረዳ/ከተማ አስተዳደሮች የሳይንስ ካፌ የማደራጀት ፍላጎትና ምቹ ሁኔታዎች መኖራቸውን ለማረጋገጥ የዳሰሳ ጥናት ይካሄዳል፤
3. የፍላጎት በቢሮውና በዞኑ/ በልዩ ወረዳው/ ከተማው በጋራ የሚከናወን ይሆናል፤
4. የዳሰሳ ጥናቱ ውጤት ለመማክርት ጉባዔው ቀርቦ ይፀድቃል፡፡

### 8. የሳይንስ ካፌዎች የሚቋቋምባቸውን አካባቢዎች መምረጫ መስፈርቶች

የሳይንስ ካፌዎችን በሁሉም የክልሉ ከተሞች ማቋቋምና ማደራጀት አስፈላጊ ቢሆንም ከፍተኛ አቅም የሚጠይቅ በመሆኑ በፍላጎት ዳሰሳ ጥናቱ መነሻ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ከተሞች ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ለመምረጥ የሚያስችል መምረጫ መስፈርት ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት መምረጫ መስፈርቱ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ለሳይንስ ካፌ ግንባታ ቦታ ማዘጋጀት የሚችል፤
2. በየዓመቱ የስራ ማስኬጃ በጀት ለመመደብ ያለው ቁርጠኝነት፤
3. አስፈላጊ የሆነ የሰው ኃይል ለማሟላት ያለው ፈቃደኝነት፤
4. አስፈላጊ መሰረተ ልማት መኖር /ኢንተርኔት፤ውሀ፤ መብራት ወዘተ.
5. ት/ቤቶች፤ ዩኒቨርሲቲ፤ ኮሌጅ በአቅራቢያ መኖር፤
6. ከተማው በክልሉ የተሰጠው ደረጃ ወይም ፈርጅ፤
7. እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች መስፈርቶች ሊካተቱ ይችላሉ፡፡

### 9. ካፌ የሚደራጅባቸው አካባቢዎች አመራረጥ ስርዓት

የሳይንስ ካፌ ወጣቶችን ማዕከል ያደረገ በመሆኑ በከተማው በሚገኘው የወጣቶች ማዕከል ግቢ ውስጥ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ሌሎች ማህበረሰቦችንም በተለይም ተመራማሪዎችንና የፈጠራ ሰዎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ት/ቤቶች፤ ዩኒቨርሲቲዎች፤ ኮሌጆች በአቅራቢያ በሚገኙበት አካባቢ መሆን ይኖርበታል፡፡

### 10. የተለዩ አካባቢዎችን ማሳወቅ፤

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 መሰረት ለሳይንስ ካፌ ማቋቋሚያ የተለየውን ለፍራ ዞኑ ወይም ልዩ ወረዳው ለቢሮው በደብዳቤ ያሳውቃል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ማቋቋምና አደረጃጀትን በተመለከተ

### 11. መሠረተ ልማትና ፋሲሊቲ

ዞኑ ወይም ልዩ ወረዳው ወይም ከተማ አስተዳድሩ ለሳይንስ ካፌው የሚሆን መሰረተ ልማት ማለትም መንገድ፣ ኢንተርኔት መስመር፤ ውሀ፤ መብራት ወዘተ ያቀርባል፡፡

### 12. የውስጥ ቁሳቁስ ስለማሟላት

1. ቢሮው ለሳይንስ ካፌው የሚሆን ቁሳቁስ ያቀርባል፤ ለዞኑ /ልዩ ወረዳው/ከተማ አስተዳድሩ በህጋዊ መንገድ ያስረክባል፤
2. ዞኑ ወይም ልዩ ወረዳው ወይም ወረዳው/ከተማ አስተዳድሩ የተረከበውን ቁሳቁስ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

### 13. ለካፌው የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

1. የኢንተርኔት አገልግሎት ለመስጠት የሚያገለግሉ መሳሪያዎች፤
2. ለዲጂታል ቤተ መጽሐፍት አገልግሎት የሚሰጡ ኮምፒውተሮች የተለያዩ መፅሐፍት፣ ዲጂታል መፅሐፍት፣ ሳይንሳዊ የሆኑ አስተማሪ ቪዲዮዎች፣ እንደ አስፈላጊነቱም አረንጓዴ ስፍራዎችን ያካትታል፡፡
3. ለሳይንስ ውይይትና ግንዛቤ ማዳበሪያ የሚያገለግሉ የኦድዮቪዥዋል መሳሪያዎች፣ ምቹ ወንበሮች፣ ጠረጴዛ፣ የመጽሐፍት መደርደሪያ ወዘተ.
4. የኪችን ቁሳቁሶች፡- ኪችን ካቢኔት፣ ለሻይ ቡና እና ለፈጣን ምግቦች አገልግሎት የሚውሉ ቁሳቁሶች፤ ፍሪጅ፣ ስቶቭ ኦቨን ወዘተ፤
5. ለሥልጠና እና ለውይይቶች የሚያስፈልግ ምቹ የመወያያ ክፍል፣ ፕሮጀክተር፣ ሳይንሳዊ መጽሔቶች እና ሌሎች፤

### 14. የአገልግሎት ማሻሻልና ተቋማዊ ማስፋፊያን በተመለከተ፤

እንደ ወቅቱ ሁኔታ በሳይንስ ካፌው የሚሰጡ አገልግሎቶችን የማሻሻል ወይም የማስፋፋት ኃላፊነት የዞኑ/ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ/ከተማ አስተዳድሩ እና በቢሮው በጥናት ላይ የተመሰረተ የጋራ ውሳኔ ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

## ተግባርና ኃላፊነት

### 15. የመማክርት ጉባዔው ተግባርና ኃላፊነት

የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መማክርት ጉባዔው አደረጃጀትና አሠራር መመሪያ የተሠጠው ስልጣንና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ የሚቋቋሙ የሳይንስ ካፌዎችን አስመልክቶ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. ዓመታዊ የሳይንስ ካፌዎች የማቋቋሚያ ዕቅድ በሚገባ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ፤
2. ካፌዎች የሚቋቋምባቸው አካባቢዎች ፍትሐዊና ግልጽ በሆነ ስርዓት መመረጣቸውን መከታተል፤
3. በዚህ ተግባር ተሳታፊ የሚሆኑ አካላት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤ አፈጻጸማቸውንም ይገመግማል፤
4. ለተግባሩ የሚያስፈልግ በጀት በወቅቱ እንዲመደብ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙንም ይገመግማል፤
5. የሚቋቋሙት ካፌዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን፤ ፍትሐዊ አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸውንና በወጣቶች ስብዕና ግንባታ ላይ ያመጡትን ለውጥ ይገመግማል፤ የማስተካከያ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል።

### 16.የቢሮው ተግባርና ኃላፊነት

1. የካፌዎች አደረጃጀትና አስተዳደር የአሰራር መመሪያ ያዘጋጃል ፤አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ያሻሽላል፤
2. የካፌዎች የማቋቋሚያ ዕቅድ ያዘጋጃል፤ በጀት ያስመድባል።
3. ለሚቋቋሙ የሳይንስ ካፌዎች በመነሻ ደረጃ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ማሟላት ማለትም፡- ዲጂታል ቤተ መጽሐፍት፣ ለቤተ-መጽሐፍት ግልጋሎት የሚሰጡ ኮምፒውተሮች፤ የተለያዩ መፅሐፍት በሶፍት-ቅጂ፣ ሳይንሳዊ የሆኑ አስተማሪ ቪዲዮዎች፣ ዌልፍ እና የኢንተርኔት አገልግሎቶችን የሚሰጡ መሳሪያዎችን ማሟላት እና መስመሮቹን መዘርጋት፤ የመወያያና የስልጠና ክፍል፣ የካፍቴሪያ አገልግሎቶችን መስጫ በግብዓት ማሟላት፤
4. በቀጥታይነት በሳይንስ ካፌው የሚካሄዱ የመማማሪያ መድረኮችን በሙያ እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ በገንዘብና ቁሳቁስ መደገፍ፤
5. ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የሳይንስ ካፌዎች እንዲጠናከሩ ተቀናጅቶ መስራትና ድጋፍ ማድረግ፤
6. የማቋቋም ተግባሩን በበላይነት ይመራል፤ ባለድርሻ አካላትንም ያስተባብራል።

7. በሳይንስ ካፌዎች ዓላማ፣ አስተዳደርና አጠቃቀም ዙሪያ ለሚያስተዳድሩ አካላት ስልጠናዎችን ይሠጣል፡፡

8. የሪፖርት ማጠናቀሪያ ቅጽ በማዘጋጀት በየሩብ ዓመቱ ሪፖርት ተቀብሎ ያደራጃል፤ ለሚመለከተው አካልም ያስተላልፋል፡፡

9. የካፌዎችን አጠቃቀምና አስተዳደር አስመልክቶ በየወቅቱ ክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ በማድረግ ግብረ መልስና ሪፖርት ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፡፡

10. በካፌዎች ተገቢ የንብረት አስተዳደር ስርዓት እንዲኖር ያደርጋል፤ ወቅታዊ የንብረት ቆጠራ ሪፖርት ተቀብሎ ክፍተቶች ሲኖሩ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

11. ከመማክርት ጉባዔውና ከክልሉ መንግስት የሚሠጡትን ተጨማሪ ተግባራት ያከናውናል፡፡

## 17. የዞን/ልዩ ወረዳ አስተዳደር ተግባርና ኃላፊነት

1. ለግንባታ የሚሆን ቦታ በማዘጋጀት ያቀርባል፡፡

2. የውሃ፣የመንገድና የኤሌክትሪክ መሰረተ ልማቶችን ያመቻቻል፡፡

3. አገልግሎት የሚሠጡ ሰራተኞችን በቋሚነት በመመደብ ብቁና ውጤታማ አገልግሎት እንዲሠጥና አስተማማኝ ጥበቃ እንዲኖር ያደርጋል፡፡

4. በየዓመቱ የስራ ማስኬጃ በጀት ከዞን/ልዩ ወረዳው አስተዳደር ያስመድባል፤

5. የንብረት ቆጠራ በማከናወን ወቅታዊ ሪፖርት ለቢሮው ያቀርባል፡፡

6. የካፌውን አፈጻጸም የሚመለከት ወቅታዊ ሪፖርት ተዘጋጅቶ በሚቀርብለት ቅጽ መሠረት በማዘጋጀት በሴቶች ፣ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ መዋቅር አማካይነት ለቢሮው ያቀርባል፤ በሚሰጠው ግብረ መልስ መሠረት የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

7. የካፌዎችን አገልግሎት አሠጣጥ ለማሳደግና ዘመኑ የወጣቶችን ፍላጎት እርካታ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራትን በቀጣይነት ያከናውናል፡፡

8. ወቅታዊና ቀጣይነት ያለው የዕድሳት፣ የአካባቢ ጥበቃና የማስዋብ ተግባራትን ለማከናወን በጀት ያስይዛል፤ በትኩረት ያከናውናል፡፡

9. ከመማክርት ጉባዔውና ከመንግስት የሚሠጡትን ተጨማሪ ተግባራት ያከናውናል፡፡

## 18. የሳይንስ ካፌው ተግባርና ኃላፊነት

1. የሳይንስ ካፌውን ደህንነትና አስፈላጊውን ጥበቃ ያካሂዳል፤
2. አጠቃላይ የሳይንስ ካፌውን የትግበራ ዓመታዊ ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ያጸድቃል፤ ይተገብራል፤
3. የሳይንስ ካፌው ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጥ ያስተዳድራል፤ ይመራል፤
4. የአስተዳደር እርከኑን በመጠበቅ የአፈፃጸም ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## ክፍል አምስት

## አስተዳደርና ጥበቃን በተመለከተ

### 19. አጠቃቀምን በተመለከተ

የሳይንስ ካፌዎች የወጣቶችን ስብዕና በመገንባት ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ያላቸውን ዝንባሌ የሚያሳድጉበትና በዘርፉ አቅማቸውን ለመገንባት የሚያስችሉ ስራዎች ብቻ የሚሰሩበት ማዕከል ነው፡፡ በመሆኑም ከሳይንስና ቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ጋር በቀጥታ ከሚገናኙ ጉዳዮች ውጪ መጠቀም አይቻልም፡፡

### 20. የንብረት አስተዳደር

በካፌዎች ያሉ ንብረቶች አስተዳደር በክልሉ የመንግስት ንብረት አስተዳደር ስርዓት መሠረት ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን የሚከተሉትን አሰራሮች ይከተላል፡-

1. እያንዳንዱ ንብረት በቋሚነት በተመደበ የካፌው ስራተኛ ስም ተመዝግቦ ወጪ ሊደረግ ይገባል፡፡
2. ንብረቶችን በስሙ ወጪ ያደረገው ሰራተኛ በንብረቶቹ ብልሽትም ይሁን መጥፋት ተጠያቂ ይሆናል፡፡
3. አጠቃላይ የንብረት ቆጠራ በየስድስት ወሩ በማከናወን ወቅታዊ ሪፖርት ለሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮና ለሚመለከታቸው አካላት ይላካል፡፡
4. ማንኛውንም ንብረት ለሌላ አካል ማዋስም ሆነ ከካፌው ውጪ ጥቅም ላይ እንዲውል መደረግ የለበትም፡፡

### 21. የሰው ሃብት ማሟላት

ዞን/ወረዳ/ልዩ እና ወረዳ/ከተማ አስተዳደሮች ካፌዎች ተገቢውን አገልግሎት በተሟላ ሁኔታ መስጠት የሚያስችላቸውን የሰው ኃይል መደበኛ በሆነ መዋቅር የሚያሟሉ ይሆናል፡፡ በመሆኑም የቤተ መጻሕፍ ባለሙያ፣ የካፌው አስተናጋጅ፣ የካፌው ሃላፊ /የአስተዳደር/፣ የአይሲቲ ባለሙያ፣ የጽዳትና የጥበቃ ሠራተኞች በቋሚነት የሚመደቡ ይሆናል፡፡

### 22. ከአገልግሎት ስለሚገኝ ገንዘብ

ካፌዎች በሽያጭ ከሚያቀርቧቸው አገልግሎቶች የሚገኙ ገቢዎች የመንግስት ገቢ አሰባሰብና አስተዳደር ስርዓትን የሚከተሉ ሲሆን አጠቃቀማቸውም ህጋዊ አሰራርን ጠብቆ የአስተዳደር ወጪያቸውን ለመሸፈንና የማስፋፊያ ተግባራትን ለማከናወን የሚውል ይሆናል፡፡

### 23. ክትትልና ድጋፍ

የሳይንስ ካፌዎች በሳይንስና ቴክኖሎጂ አቅም ግንባታና የወጣቶች ስብዕና ግንባታ ጋር በተያያዘ የሚያከናውኗቸው ተግባራት ከተቋቋሙለት ዓላማና ክልላዊ የሳይንስ፣ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ልማትን

ማረጋገጥ በሚያስችል ሁኔታ እንዲመራ ለማስቻል ክቢሮው ድጋፍ፣ክትትልና ግምገማ ይደረግላቸዋል፡፡

**24.የተገልጋዮች መብትና ግዴታ**

**1. የተገልጋዮች መብት**

ሀ/ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ያለምንም አድልዎና ልዩነት በካፌው የመጠቀም መብት አለው፡፡

ለ/ መጽሐፍት ለማንበብና የተለያዩ ኮንፈረንስ ለመሳተፍ ክፍያ አይጠየቁም፡፡

መ/ መረጃ የመጠየቅና የማግኘት መብት

ሠ/ አስተያየትና ቅሬታ የማቅረብ እና ምላሽ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

ረ/ ለከፈሉት ገንዘብ ደረሰኝ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

**2. የተገልጋዮች ግዴታ**

ሀ/ መታወቂያ የመያዝና በተጠየቁ ጊዜ ሁሉ የማሳየት ወይም የማስያዝ ግዴታ አለባቸው፡፡

ለ/ ንብረቶችን በአግባቡ የመጠቀምና በአጠቃቀም ችግር ለሚደርስ ጉዳት ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

መ/ የሌሎች ተገልጋዮችን መብት ማክበር፡፡

ሠ/ በክፍያ ለሚሠጡ አገልግሎቶች ተገቢውን ክፍያ መፈጸም፡፡

ረ/ የተቋሙን ህግና ደንብ ማክበር፡፡

**25.ጥብቅ ክልከላ ስለተደረገባቸው ጉዳዮች**

1. የፖለቲካ ልሳናት እና ሀይማኖታዊ የሆኑ ጽሑፎችን ማስነበብ፤
2. የመንግስት፣ የፖለቲካ ድርጅት እንዲሁም የሌሎች አደረጃጀቶችን ስብሰባ ማካሔድና እንዲካሔዱ መፍቀድ፤
3. ጫት ማስቃም፣ አደንዛዥ ዕጾች እንዲጠቀሙ መፍቀድና አልኮል መጠጦችን መሸጥ፤
4. የእግር ኳስና ሌሎች ከሳይንስና ቴክኖሎጂ አቅም ግንባታና አዕምሮ ብልጽግና ጋር ቀጥታ ተያያዥነት የሌላቸውን የመዝናኛ ፕሮግራሞችን ማሳየትና ማጫወት፤
5. የእስፖርት እንቅስቃሴ ልምምዶችና ተውኔቶች ማካሔድና እንዲካሔዱ መፍቀድ፤

**26.በካፌው ስለሚሠጡ አገልግሎቶች**

የሳይንስ ካፌዎች የወጣቶች የሳይንስና ቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ማዕከላት በመሆናቸው የሚከተሉትን አገልግሎቶች የሚሠጡ ይሆናል፡-

1. የሳይንስና ቴክኖሎጂ መጻሕፍት ንባብ /የቤተ መፃህፍት አገልግሎት፤
2. በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዙሪያ የተጻፉ መጻሕፍትና መረጃዎች ዲጂታል ላይበራሪ፤
3. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮንፈረንስ ማካሔድ፤

4. በሳይንስና ቴክኖሎጂ የምርምርና የፈጠራ ስራ ውጤት ባለቤት ምሁራንና ወጣቶችን በመጋበዝ ጥናታዊ ጽሑፎችን እንዲያቀርቡ ማድረግ፤

5. የሳይንስና ቴክኖሎጂ አውደ ርዕይ ማካሔድ፤

6. በአካባቢ ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎችና ትምህርት ቤቶች ጋር በመተባበር የሳይንስ ሳምንታት ፕሮግራሞችን ማሰናዳትና ወጣቶች እንዲያከብሩ ማድረግና መሰል አገልግሎቶች፤

7. የምግብ፣ ትኩስና ለስላሳ መጠጥ አቅርቦት፤

8. የካፊቴሪያ አገልግሎት/ፈጣን ምግቦች፣ ሻይ፣ ቡና፣ እና ለስላሳ መጠጦችን በተመጣጣኝ ዋጋ የሚያቀርብ ይሆናል።

**27.የአገልግሎት መስጫ ጊዜ**

ሁሉም ሳይንስ ካፌዎች ከበዓል ቀናት ውጪ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 4:00 ሰዓት አገልግሎት የሚሠጡ ይሆናል።

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**28. ተጠያቂነት**

ይህንን መመሪያ በመተላለፍ ያልተፈቀደ ነገር የፈጸመ የትኛውም አካል በመደበኛው የህግ አግባብ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**29. መመሪያውን ስለማሻሻል**

1. ይህንን የአሰራር መመሪያ ቢሮው እንዲሻሻል ባመነበት ጊዜ ሁሉ ሊያሻሽለው ወይም ሊለውጠው ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ የንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በቢሮው መመሪያው በተሻሻለ በማናቸውም ጊዜ ለፍትህ ቢሮ መመሪያው የተሻሻለ ስለመሆኑ በማሳወቅ ማስመዘገብና ቁጥር እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፡፡

**30. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በክልሉ የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ ጸድቆ በክልሉ ፍትህ ቢሮ ከተመዘገበበት ጥር 5 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ሰላሙ አማዶ

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ ኃላፊ

## አባሪ 1

### ለሳይንስ ካፌዎች የሚያስፈልጉ ቋሚ ሰራተኞች ፍላጎት ማሳያ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የመደብ መጠሪያ | የት/ት ዝግጅት | የሥራ ልምድ | ደረጃ | ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ስራ አስኪያጅ | የመጀመሪያ ዲግሪ | | 12 | 1 | |
| 2 | ሁሰገብ የኮምፒዩተር ባለሙያ | አይ.ሲ.ቲ ፣ ደረጃ 4 | | 11 | 2 | |
| 3 | ተገልጋይ ተቀባይና መረጃ ጥንቅር ባለሙያ | ሴክሬቴሪያ ሳይንስ ፣ ደረጃ 4 | | 8 | 2 | |
| 4 | የቤተ መጽሐፍት ባለሙያ | ላይብራሪ ሳይንስ ፣ ደረጃ 4 | | 8 | 4 | |
| 5 | ጥበቃ | | | 3 | 2 | |
| 6 | የግቢ ውበትና አትክልተኛ | | | 2 | 2 | |
| 7 | የጽዳት ሰራተኛ | | | 1 | 2 | |
| | | | | ጠቅላላ | 15 | |

## አባሪ 2፡- የሳይንስ ካፌዎች ቋሚ ሰራተኞች የስራ መዘርዝር፣ መስፈርትና የመደብ ብዛት

### 2.1 የሳይንስ ካፌው ስራ አስኪያጅ

| ተ.ቁ | የክንዋኔ ቅደም ተከተል | የስራዉ ክንዋኔ በስፋትና በአቅጣጫ ማደራጀት | የሚያስፈልግ የት/ደረጃ የስራ ልምድና ሙያ መስመር | ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የካፌውን አመታዊ ዕቅድ ያዘጋጃል | ከተራ ቁጥር 1 እስከ 10 የተዘረዘሩ ተግባራት በካፌው ስራ አስኪያጅ የሚሠሩ ይሆናል | የመጀመሪያ ዲግሪ በማኔጅመንት፣ አካውንቲንግ፣ ኢኮኖሚክስ፣ ምህንድስና | 1 |
| 2 | ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ሳይናሳዊ ትብብር እንዲፈጠር ይሰራል | | | |
| 3 | የተቋሙን ሰራተኞች ይመራል፣ ያስተባብራል | | | |
| 4 | የተቋሙን አገልግሎት ማሻሻያ ዕቅዶች ያዘጋጃል፣ተግባራዊ ያደርጋል | | | |
| 5 | በተቋሙ ዓላማና ተልዕኮ ዙሪያ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ይሰራል | | | |
| 6 | የካፍቴሪያ አገልግሎት በአስተዳደር መመሪያው መሠረት እየተሰጠ መሆኑን ክትትል ያደርጋል | | | |
| 7 | ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ሳይንሳዊ ኮንፈረንሶችና አውደ ርዕዮችን ማዘጋጀትና ሒደቱን መምራት | | | |
| 8 | ከአካባቢው የትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሳምንታት እንዲከበሩ ያደርጋል | | | |
| 9 | ወቅታዊ ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል | | | |
| 10 | ከቢሮውና የበላይ አካላት የሚሰጡትን ስራዎች ይሰራል | | | |

## 2.2 ሁለ ገብ የኮምፒውተር ባለሙያ

| ተ.ቁ | የክንዋኔ ቅደም ተከተል | የስራዉ ክንዋኔ በስፋትና በአቅጣጫ ማደራጀት | የሚያስፈልግ የት/ደረጃ የስራ ልምድና ሙያ መስመር | ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ወቅታዊ የሳይንስ፣ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን መጻህፍት መጫን | ከተራ ቁጥር 1 እስከ 7 የተዘረዘሩ ተግባራት በሁለገብ የኮምፒውተር ባለሙያ የሚሠሩ ይሆናል | በICT በ12+2 ዲፕሎማ ወይም በደረጃ 4 የተመረቀ/ች | 2 |
| 2 | የተገልጋዮችን የኮምፒውተር አጠቃቀም መከታተልና ድጋፍ ማድረግ | | | |
| 3 | ተገቢ የኢንተርኔት አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ | | | |
| 4 | ለኮምፒውተሮችና አዲዮቪዡዋል መሳሪያዎች ወቅታዊ ቅድመ መከላከል ጥገና ማድረግ | | | |
| 5 | በተቋሙ የሚካሔዱ ኮንፈረንሶችና ሌሎች ኩነቶች ላይ ተገቢው የሙያ ድጋፍ ማድረግ | | | |
| 6 | የተበላሹ ኮምፒውተሮችንና አዲዮቪዡዋል መሳሪያዎችን መጠገንና ከአቅም በላይ የሆኑትን በመለየት የብልሽት አይነታቸውንና መጠን እንዲሁም የሚያስፈልገውን የጥገና አይነት የሚያሳይ ሙያዊ ትንተናና ሪፖርት ለስራ አስኪያጁ ማቅረብና ተጠግነው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ መከታተል | | | |
| 7 | ከኃፊው ስራ አስኪያጁ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል | | | |

## 2.3 ተገልጋይ ተቀባይና የመረጃ ጥንቅር ባለሙያ

| ተ.ቁ | የክንዋኔ ቅደም ተከተል | የስራዉ ክንዋኔ በስፋትና በአቅጣጫ ማደራጀት | የሚያስፈልግ የት/ደረጃ የስራ ልምድና ሙያ መስመር | ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ተገልጋዮችን መቀበልና መረጃ መስጠት | ከተራ ቁጥር 1 እስከ 7 የተዘረዘሩ ተግባራት በተገልጋይ ተቀባይና መረጃ ጥንቅር ባለሙያ የሚሠሩ ይሆናል። | በሴክሬተሪያል ሳይንስ በ12+2 ዲፕሎማ ወይም በደረጃ 4 የተመረቀ/ች | 2 |
| 2 | የተገልጋዮችን አስተያየት እየተቀበሉ በሪፖርት ፎርማት በማጠናቀር በየወቅቱ ለስራ አስኪያጁ ማቅረብ | | | |
| 3 | የተገልጋዮችን መረጃ በየዕለቱ በመመዝገብ ማደራጀት | | | |
| 4 | የተቋሙን ደንብና ስርዓት ማስከበር | | | |
| 5 | ወቅታዊ የአገልግሎት አሠጣጥ ሪፖርት በማዘጋጀት ለስራ አስኪያጁ ያቀርባል | | | |
| 6 | ገቢና ወጭ የተደረጉ ደብዳቤችን፣ መረጃዎችንና ማህደሮችን ዕለታዊ እንቅስቃሴ ይቀበላል፣ይመዘግባል፣ያደራጃል፣ ስታትስቲካዊ መረጃዎችን ሪፖርት ያደርጋል። | | | |
| 7 | ከኃፊው ስራ አስኪያጅ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል | | | |

## 2.4 የቤተ መጽሐፍ ባለሙያ

| ተ.ቁ | የክንዋኔ ቅደም ተከተል | የስራዉ ክንዋኔ በስፋትና በአቅጣጫ ማደራጀት | የሚያስፈልግ የት/ደረጃ የስራ ልምድና ሙያ መስመር | ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የመረጃ ምንጮችን በኮምፒዩተር በመታገዝ የካታሎጊንግ ሥራ ያከናውናል፡፡ | ከተራ ቁጥር 1 እስከ 12 የተዘረዘሩ ተግባራት በቤተ መጽሐፍ ባለሙያ የሚሠሩ ይሆናል፡፡ | በላይብራሪ ሳይንስ በ12+2 ዲፕሎማ ወይም በደረጃ 4 የተመረቀ/ች | 2 |
| 2 | በቤተ መጻህፍቱ ለሚገኙ የመረጃ ምንጮች የክላሲፊኬሽን ሥራ ይሠራል፡፡ | | | |
| 3 | በሥራ ዘርፉ ለሚታይ የአሰራር ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት በሚደረግ የዳሰሳ ጥናት አስፈላጊ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ያደራጃል፡፡ | | | |
| 4 | የቤተ መጻህፍቱ አገልግሎት ምቹ እንዲሆን የወንበሮችንና ጠረጴዛዎችን አቀማመጥ ያስተካክላል ፤ ጽዳታቸውና ደህንነታች እንዲጠበቅ ያደርጋ፡፡ | | | |
| 5 | በቤተ መጻህፍቱ ውስጥ የሚገኙ የመረጃ ምንጮች እንዳይበላሹና እንዳይጠፉ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ያደርጋል፡፡ | | | |
| 6 | በሥራ ዘርፉ የሚታዩ የአሰራር ችግሮች እንዲሻሻሉ በመፈተሽ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፡፡ | | | |
| 7 | የመጻህፍት የውሰትና ንባብ አገልግሎት ይሰጣል፣ በወቅቱ መመለሳቸውን ይከታተላል፡፡ | | | |
| 8 | ቤተመጻህፍቱ በወቅታዊ መረጃ የተሟላ እንዲሆን በመረጃ መረጣ ላይ ይሳተፋል፡፡ | | | |
| 9 | አስፈላጊ ስታትስተካዊ መረጃዎችን ያጠናቅራል፡፡ | | | |
| 10 | ድጋፍና እገዛ ለሚያስፈልጋቸው ተገልጋዮች አስፈላጊውን እገዛና ድጋፍ ይሰጣል፡፡ | | | |
| 11 | ለተገልጋዮች E-Resources እንዲጠቀሙ ያደርጋል፡፡ | | | |
| 12 | ከኃላፊው ስራ አስኪያጅ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል | | | |

Central Ethiopia Regional State Science & Information Technology Bureau

## 2.5 የግቢ ውበትና አትክልተኛ

| ተ.ቁ | የክንዋኔ ቅደም ተከተል | የስራዉ ክንዋኔ በስፋትና በአቅጣጫ ማደራጀት | የሚያስፈልግ የት/ደረጃ የስራ ልምድና ሙያ መስመር | ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የአትክልት ሥፍራዎችን ይኩተኩታል፣ ውሃ ያጠጣል፣ ልዩ ልዩ አትክልቶችን፣ አበባዎችንና ዛፎችን ይተክላል፣ ያስተካክላል፣ ይንከባከባል፤ | ከተራ ቁጥር 1 እስከ 9 የተዘረዘሩ ተግባራት በግቢ ውበትና አትክልተኛ የሚሠሩ ይሆናል | | 2 |
| 2 | የመሥሪያ ቤቱን ምድረ ግቢና የአትክልት ሥፍራዎችን በንጽሕና ይይዛል፣ ይጠብቃል፣ በመንገድ ላይ የሚበቅሉ ሳሮችን፣ አረሞችንና ሌሎች ባዕድ ነገሮችን ያስወግዳል፤ | | | |
| 3 | ለዕዋት ጥሩ ዕድገት እንዲኖራቸው ማዳበሪያ መጥኖ ይጨምራል፣ እንደ አስፈላጊነቱም ፀረ ተባይ መድኃኒት ይረጫል፤ | | | |
| 4 | የአትክልት ሥፍራዎች በሰዎችና በእንስሳት እንዳይረገጡ፣ አትክልትና አበባዎች እንዳይቆረጡ ይከላከላል፤ | | | |
| 5 | የእጅ ማጭድ ወይም የማጨጃ ማሽን በመጠቀም ሣር ያጭዳል፤ | | | |
| 6 | ዛፎችን፣ አትክልትንና አበባዎችን ይገርዛል፣ የተተከሉ ዛፎችን በመከርከም ቅርጽ ያወጣል፤ | | | |
| 7 | የችግኝ ማፍያ መደቦችን ያዘጋጃል፣ የተክልና የአበቦች ዓይነት በመምረጥ ችግኞችን ያራባል፣ ይተክላል፤የተለያዩ ተክሎችና አበባዎችን ጎንድ በመቁረጥ ያዳቅላል፤ | | | |
| 8 | ለሥራ የሚጠቀምባቸውን መሣሪያዎች በጥንቃቄ ይይዛል፣ ሲበላሹ ወይም ከአገልግሎት ውጭ ሲሆኑ ለኃላፊው ያሳውቃል፤ | | | |
| 9 | ከኃፊው ስራ አስኪያጅ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል | | | |

## 2.6 የጽዳት ሰራተኛ

| ተ.ቁ | የክንዋኔ ቅደም ተከተል | የስራዉ ክንዋኔ በስፋትና በአቅጣጫ ማደራጀት | የሚያስፈልግ የት/ደረጃ የስራ ልምድና ሙ-ያ መስመር | ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የቢሮዎችን፣ የስብሰባ አዳራሾችን መድረኮችን፣የላይብረሪዎችን፣ የመፀዳጃ ቤቶችን፣ ወለል፣ ኮርኒስ፣ ኮሪደር፣ ግድግዳና መስተዋቶችን ያጸዳል፤ | ከተራ ቁጥር 1 እስከ 9 የተዘረዘሩ ተግባራት በጽዳት ሰራተኛ የሚሠሩ ይሆናል | | 2 |
| 2 | በስራ ክፍሉ ውስጥ የሚገኙ ኮምፒተር ፕሪንተር ጠረጴዛዎችና ወንበሮችና መደርደሪያዎች ይወለውላል፤ ተዘበራርቀው የነበሩ ወረቀቶችን ሰብስቦ ግልጽ በሆነ ቦታ ያስቀምጣል፡፡ | | | |
| 3 | በተቋሙ የንብረት ክፍል የተከማቹ ዕቃዎችና መደርደሪያዎችን አቧራ ያፀዳል፣ የሸረሪት ድርና የሌሎች ቆሻሻዎች ይጠርጋል፣ የተፋሰሱና የወዳደቁ ዕቃዎችን ይሰበስባል፤ | | | |
| 4 | በመጸዳጃ ቤት አገልግሎት መስጠት ያቆሙ የእጅ መታጠቢያዎችንና ፍሳሽ ማስወገጃዎች በወቅቱ እንዲጠገኑ ለሚመለከተው ክፍል ሪፖርት ያደርጋል፡፡ | | | |
| 5 | ለፅዳት ስራ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችና ሌሎች አስፈላጊ የጽዳት እቃዎች በወቅቱ ተሟልተው እንዲገኙ ጥያቄ ያቀርባል፤ሲሟሉም ለጽዳት አገልግሎት ያውላል፡፡ | | | |
| 6 | የስራ መገልገያ መሳሪያዎችና አልባሳት በጥንቃቄና ንጽህና በመያዝ በአግባቡ አገልግሎት ላይ ያውላል፡፡ | | | |
| 7 | በክፍሉ ውስጥ የሚገኙ መጋረጃዎች እና የቢሮ ምንጣፎችን ያጥባል፡፡ | | | |
| 8 | ቆሻሻዎችን በመሰብሰብ ወደተገቢው በማጠራቀሚያ ቦታ ወስዶ ይደፋል፣ ያቃጥላል፤ | | | |
| 9 | ከኃፊው ስራ አስኪያጅ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል | | | |

## 2.7 ጥበቃ

| ተ.ቁ | የክንዋኔ ቅደም ተከተል | የስራዉ ክንዋኔ በስፋትና በአቅጣጫ ማደራጀት | የሚያስፈልግ የት/ደረጃ የስራ ልምድና ሙያ መስመር | ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በሚወጣለት መመሪያና ፕሮግራም መሰረት የተቋሙን ንብረትና ሰራተኛ ደህንነት በንቃት ይጠብቃል፤ | ከተራ ቁጥር 1 እስከ 10 የተዘረዘሩ ተግባራት በጥበቃ ሰራተኛ የሚሠሩ ይሆናል | | 2 |
| 2 | ወደውጭ የሚወጡ የተቋሙን ንብረትና ተሽከርካሪዎች በሚመለከተው ሃላፊ የተፈቀደ መሆኑን በማረጋገጥ ያሳልፋል፤ | | | |
| 3 | ወደተቋሙ የሚመጡ እንግዶች በስነ ስርዓት ያስተናግዳል፤ ፈትሾ ያስገባል፤ | | | |
| 4 | ከሥራ ሰዓት ውጭ የተቋሙ ስራ ክፍሎች½ መስኮቶች መቆለፋቸውን፤ መብራትና ውሃ መዘጋታቸውን ያረጋግጣል፤ | | | |
| 5 | ወደ ግቢ የሚገቡ መሳሪያ የያዙ ተገልጋዮችን በመቀበል መለያ ካርድ መስጠትና ሲወጡ ካርዱን በመቀበል መሳሪያቸውን ይመልሳል፤ | | | |
| 6 | ከጥበቃው ተራ እለት የሥራ ሰዓቱን አክብሮ ምድብ ስራው ላይ በመገኘት ከተቀያሪው ጋር የንብረት ርክክብ ያደርጋል፤ ከሥራ ሲወጣም ቁጥሮ ለተረኛ ያስረክባል፤ | | | |
| 7 | የጥበቃ መሣሪያዎችን በጥንቃቄና በእንክብካቤ ይይዛል፤ መሣሪያዎች ለመሥሪያ ቤቱ ጥበቃ ተግባር ብቻ ያውላል፤ | | | |
| 8 | በተቋሙ ውስጥ ሁከት፤ የፀጥታ መደፍረስና የወንጀል አደጋ ሊፈጥሩ የሚችሉ ሁኔታዎች እንዳይከሰቱ ቅድመ ጥንቃቄ ያደርጋል፤ ችግሮች ሲፈጠሩ ለማረጋጋት ይሞክራል፤ ችግር ፈጣሪዎችን በመለየት ለኃላፊው ያሳውቃል፤ | | | |
| 9 | የእሳት አደጋ ሲፈጠር ለማጥፋት ይሞክራል፤ ከአቅሙ በላይ ሲሆን የእሳት አደጋ መከላከያን በስልክ ይጠራል፤ | | | |
| 10 | ከኃፊው ስራ አስኪያጅ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል | | | |

Central ... Regional State Science ... Information Technology Bureau